# በማህበራዊና በጤና ዘርፍ ለተሰማሩ ጋዜጠኞች የቀረበ የሽልማት ውድድር ማስታወቂያ

ድርጅታችን ዲኬቲ ኢትዮጵያ መንግስታዊ ያልሆነና ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ በተለይም በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዘርፍ በዕቅድ የተመራ ቤተሰብ እንዲኖር በማሰብ የተለያዩ አማራጮችን በመላ ሀገሪቱ በማዳረስ ላይ ይገኛል ። ይህንኑ እንቅስቃሴውን ከግብ ለማድረስ እና በሀገር ደረጃ የተቀመጡ ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ በአጋርነት እየሰራም ይገኛል ። ከዚህ ጎን ለጎንም ማህበራዊ ግዴታውን ለመወጣት ይረዳ ዘንድ በመላው ሀገሪቱ የሚገኙና በተለይም በጤናና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ጋዜጠኞችን ያበረታታል ። በያዝነው ዓመትም ህብረተሰባችን ከመገናኛ ብዙኃኑ ስለ ቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች ማግኘት ያለበትን መረጃ ለማስፋት በማሰብ ጋዜጠኞች በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲበረታታና ስራቸውንም ለውድድር እንዲያቀርቡ ዕድሉን አመቻችቷል ።

**የውድድር መስፈርቶች**

1. ተወዳዳሪው ለውድድር የሚያቀርበው ሥራ በቤተሰብ ዕቅድ ላይ ብቻ ያተኮረ ( ለምሳሌ በእናቶችና ሕጻናት ጤና ላይ ፣ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ከማኅበረሰብ ዕድገትና ከሰብዓዊ መብት ግንዛቤ ከመፍጠር አንጻር ፣ ከቤተሰብ አገልግሎት ፣ ከማኅበረሰብ ዕቅድ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ያሉ የተዛቡ አመለካከቶችን ከማጥራት አኳያ ፣ ካልተፈለገና ካልታቀደ እርግዝና አንጻር ፣ ከወጣቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና አንጻር እና በሌሎችም ይህን መሰል ይዘት ባላቸው ጉዳዮች ) መሆን አለበት ።
2. ተወዳዳሪው በማኅበራዊና ጤና ዘርፍ በሬዲዮ ፣ በቴሌቪዥንና በኅትመት የመገናኛ ብዙኃን በመደበኛነት የሰራ ወይንም እየሰራ ያለ መሆን አለበት ። በግል ጥረታቸው በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ጣቢያዎች የዓየር ሰዓት ይዘው ወይንም በጋዜጣና መጽሄት አምድ ይዘው የሚሰሩ ጋዜጠኞች ይበረታታሉ ።
3. ተወዳዳሪው ከዚህ ቀደም በሬዲዮ ወይንም በቴሌቪዥን ጣቢያዎች የተላለፉ በጋዜጦች ወይንም በመጽሄቶች የታተሙ ሥራዎቹን/ ሥራዎቿን ለውድድር ማቅረብ አለበት ። በ2012 ዓ.ም የተሰሩ ሁለት ሥራዎችንና ለዚህ ውድድር ተብለው የተዘጋጁ ሁለት ተጨማሪ አዳዲስ ሥራዎችን ይዞ መቅረብ አለበት ።

4. ተወዳዳሪው ሥራውንና የሚያቀርበው በየትኛውም የሀገር ውስጥ ቋንቋ የተላለፈ ወይንም ሊተላለፍ የታቀደና የታተመ/ሊታተም የተዘጋጀ ቢሆንም የሥራው የአማርኛ ትርጉም ከዋናው ቅጂ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት ።
5. ተወዳዳሪው ሥራው ለሕዝብ በሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ፣ በጋዜጣ ወይንመ መጽሄት የተሰራጨ ወይንም ለመሰራጨት የተዘጋጀ ስለመሆኑ ከአሰራጪው መገናኛ ብዙኃን የጽሁፍ ማረጋገጫ ይዞ መቅረብ አለበት።
6. ተወዳዳሪው ለውድድር የሚያቀርባቸው ሥራዎች መጠን እንደሚከተለው ተዘርዝሯል ።
   6.1 ለሬዲዮ መርኃ ግብር ዝግጅት ፡ ከ5 ( አምስት ) ደቂቃ ያላነሰ እና ከ15 ( አስራ አምስት ) ደቂቃ ያልበለጠ
   6.2 ለቴሌቪዥን መርኃ ግብር ዝግጅት ፡ ከ5 ( አምስት ) ደቂቃ ያላነሰ እና ከ15 ( አስራ አምስት ) ደቂቃ ያልበለጠ
   6.3 ለኅትመት የመገናኛ ብዙኃን ፡ ከ500 ( አምስት መቶ ) ቃላት ያላነሰ አ1500 ( አንድ ሺህ አምስት መቶ ) ያልበለጠ
7. ለውድድሩ የሚቀርቡ ስራዎች ፡
   7.1 በሬዲዮ መርኃ ግብር ለሚወዳደሩ ፡ በሲዲ ( ሁለት ኮፒ ) ፣ በፍላሽ እና በኦንላይን ሆኖ ፎርማቶቹ በ MP3 ወይንም በ WAV.
   7.2 በቴሌቪዥን መርኃ ግብር ለሚወዳደሩ ፡ በ ዲቪዲ ፣ በፍላሽ ዲስክ ፣ በሀርድ ዲስክ ወይንም በኦንላይን ሆኖ ፎርማቶቹ MPEG2 , MPEG4 , MDV , AVI 1080 I/P.
   7.3 በኅትመት የመገናኛ ብዙኃን ፡ የኅትመት ሥራው ቅጂ
8. ለውድድር ዕጩ የሆኑ ሥራዎች የሚቀርቡባቸው አድራሻዎች ፡

| ተ.ቁ | አካባቢ | ስልክ | የሚገኝበት ከተማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ ዋናው መስሪያ ቤት | +251 663 22 22 | አዲስ አበባ |
| 2 | ሰሜን | 0344402299 | መቀሌ |
| 3 | ሰሜን ምዕራብ | 0331115498/0333120093 | ደሴ |
| 4 | ሰሜን ምስራቅ | 0582207578 | ባሕርዳር |
| 5 | ምዕራብ | 0478119284/0472110667 | ጅማ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | መካከል | 0221121720 | አዳማ |
| 7 | ደቡብ | 0462202665 | ሐዋሳ |
| 8 | ምስራቅ | 0251114569 | ድሬዳዋ |

**9.** የውድድር ማቅረቢያ ጊዜ **ከ ጥቅምት 6 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም** ድረስ

**10.** የመጨረሻ ዙር ዕጩ ተሸላሚዎች የሚገለጽበት ጊዜ **ኅዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም**

**11.** የውድድሩ አሸናፊዎች የሚገለጽበት ጊዜ **ኅዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም**

12. በየዘርፉ ላሉ የየውድድሩ አሸናፊዎች ከዲኬቲ ኢትዮጵያ የክብር ሽልማት፣ የገንዘብና ለሙያው አጋዥ የሆኑ የኤሌክትሮኒክስ መሳርያዎች ተሸላሚ ይሆናሉ ።

**ማሳሰቢያ ፡**

**1. ዳኞች መስፈርቱን ያሟሉ ተወዳዳሪዎችን የመምረጥ ሙሉ መብት አላቸው ።**

**2. ዲኬቲ ኢትዮጵያና ዳኞች በቂ ተወዳዳሪና ስራ ካልቀረበ ይህን ውድድር በማንኛውም ጊዜ የማቋረጥ መብት አላቸው ።**

**ዲኬቲ ኢትዮጵያ**